የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት
የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
Central Ethiopia Regional State
OFFICE OF THE PRESIDENT

ቁጥር Ref.No: ማዕ/COM 52/23
ቀን Date 02/02/2016

**ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት …… ………… ቢሮ**

**………………………**

**ጉዳዩ፡- <u>የመስተዳድር ምክር ቤት ደንብ መላክን ይመለከታል</u>**

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት መስከረም 23/2016 ዓ.ም ባካሄደው 2ኛ መደበኛ ስብሰባው የመንግስት ተሿሚዎችን ጥቅማ ጥቅምና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን ለመወሰን ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ረቂቅ ደንብ ተመልክቶ አጽድቋል፡፡

በዚሁ መሰረት መስተዳድር ምክር ቤቱ ያፀደቀውን የመንግስት ተሿሚዎችን ጥቅማ ጥቅምና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 01/2016 ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያዘን የላክን በመሆኑ ተገቢው በእናንተ በኩል እንዲፈፀም እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ሰማን ሺፋ ሌገሶ
Semman Shifa Leggeso
የርዕሰ መስተዳድርና የመስተዳድር ምክር ቤት ጽ/ቤት ኃላፊ
Office of the President & Executive Council Head

**<u>ግልባጭ</u>፣**

- ለርዕሰ/መስ/እናመስ/ም/ቤት ጽ/ቤት

**<u>ሆሳዕና</u>፣**

# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የተሿሚዎችን ጥቅማ ጥቅምና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 01/2016

## መግቢያ

የክልሉ መንግስት ብቃት እና ተነሳሽነት ያላቸውን ተሿሚዎች ለመሳብና ለተሿሚዎቹ ከስራቸዉ ሀላፊነት ደረጃ እና ባህሪይ አንፃር ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን በተለይም የመኖሪያ ቤት፣ የስልክ፣ የኢንቴርኔት፣ የህክምና እና የትራንስፖርት ወጪዎች በመንግስት መሸፈን አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመንግስት ተሿሚዎች ከሀላፊነት ሲነሱ ሊኖራቸዉ የሚችሉ ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት ያለባቸዉንና ማግኘት የሌለባቸዉን ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የክፍያ መጠኑንና አፈፃፀሙን ግልጽነትና ተጠያቂነት በተላበሰ ሁኔታ ከቅድመ ሁኔታዎቹ ጭምር መደንገግ በማስፈለጉ፣

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት የአስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸዉን ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 39 (1) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 01/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ ደንብ ተፈፃሚነት ሲባል በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "የመንግስት ተሿሚ" ማለት በህዝብ ተመርጠው ወይም በመንግስት ተሹመው በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት በሚተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በኃላፊነት የሚያገለግሉ ሆኖ፡

   ሀ. በክልል መዋቅር የክልል ርዕሰ መስተዳድር፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ አፈ-ጉባኤዎች፣ ምክትል አፈ ጉባኢዎች፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የካቢኔ አባላት ቢሮ ሀላፊዎች፣ የካቢኔ ማዕረግ ሀላፊዎች፣ ምክትል ቢሮ ሀላፊዎች፣ በምክትል ቢሮ ሀላፊ ማዕረግ ተሿሚዎች፣

   ለ. በታችኛዉ እርከኖች የዞን፣ ልዩ ወረዳ እና የወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች፣ አፈ-ጉባኤዎች፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪዎች፣ የፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣ የካቢኔ አባላት፣ የካቢኔ ማዕረግ ተሿሚዎች፣ ምክትል ሀላፊዎች፣

   ሐ. ከንቲባዎች፣ የክፍለ ከተማ አስተዳዳሪዎች፣ አፈ-ጉባኤዎች፣ ካቢኔዎች፣ የካቢኔ ማዕረግ ተሿሚዎች፣ የከተማ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣

2. "ምክትል ርዕሰ መስተዳደሮች" ማለት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ የተሾሙ ሀላፊዎች ማለት ነዉ።

3. "ጥቅማ ጥቅም" ማለት ተሿሚ የመንግስት ኃላፊዎች በዚህ ደንብ መሠረት የሚያገኙት የዓይነት ወይም የገንዘብ ክፍያ ነው።

4. "ክልል" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ነው።

## ክፍል ሁለት

## ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች

**3. ደመወዝ**

የተሿሚዎች ደመወዝ መንግስት በየወቅቱ በሚያወጣው እስኬል መሠረት የሚፈፀም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ የደመወዝ እስኬልና ጥቅማ ጥቅም ካላቸው ተቋማት ለከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት ተፈልገው የሚሾሙ ኃላፊዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በቀድሞ መሥሪያ ቤታቸው እየተከፈለ የነበረ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ከተሾሙበት መደብ ደመወዝ የተሻለ ከሆነ የሚከፈል ይሆናል፡፡

**4. ውሎ አበል እና የአልጋ ወጪ**

የውሎ አበልና የአልጋ ወጪን በሚመለከት የፌዴራልና የክልል መንግስታት ተሿሚዎች የቀን ውሎ አበል ክፍያ መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

**5. . የመኖሪያ ቤት**

5.1. ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ የብሔረሰቦች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎችና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቅም በፈቀደ መጠን ለስራቸውና ለደህንነታቸው አስጊ ያልሆነ ደረጃዉን የጠበቀ የመንግስት የመኖሪያ ቤት ከሚያስፈልገዉ የቤት ዉስጥ ዕቃ ጋር **ይዘጋጅላቸዋል**፡፡ የመንግስት የመኖሪያ ቤት ካልተዘጋጀላቸዉ ደረጃዉን የጠበቀ ቤት ከነተፈላጊ የቤት ዕቃ ጋር በመንግስት ወጭ በኪራይ ያዘጋጅላቸዋል፡፡ ተሿሚዎቹ የመኖሪያ ቤትን በራሳቸዉ መከራየት የሚፈልጉ ከሆነ ግብር የማይጣልበት ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) በየወሩ ከደመወዛቸው ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

5.2. የክልሉ ካቢኔ አባላት የቢሮ ሀላፊዎች፣ በካቢኔ ደረጃ የተሾሙ የሥራ ኃፊዎች፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የብሔረሰቦች ምክር ቤት እና የክልል ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ- ጉባኤዎች፣ ዋና ኦዲተር፣ የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር እና የዞን ዋና አስተዳዳሪዎች የመንግስት የመኖሪያ ቤት ይመቻችላቸዋል፡፡ የመንግስት የመኖሪያ ቤት ካልተዘጋጀላቸዉ ብር 20,000 (ሀያ ሺህ ብር) በየወሩ ከደመወዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

5.3. በክልል ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች፣ በምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ደረጃ በክልሉ በተለያዩ ተቋማት የተሾሙ ኃላፊዎች፣ የልዩ ወረዳ አስተዳዳሪዎች የመንግስት የመኖሪያ ቤት ካልተዘጋጀላቸዉ 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) ብር በየወሩ ከደመወዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

5.4. የዞንና ልዩ ወረዳ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎች፣ የዞንና ልዩ ወረዳ ምክትል አስተዳዳሪዎች የመንግስት ቤት ካልተዘጋጀላቸዉ በየወሩ ብር 5,000.00 (አምስት ሺህ) ከደመዉዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

5.5. ቤተሰቦቻቸዉ ከክልሉ ዉጭ ቤት ተከራይተዉ እየኖሩ ያሉ ሆነዉ በከፍተኛ የሀላፊነት ቦታ ላይ የተሾሙ ሀላፊዎች ቤተሰቦቻቸዉ ባሉበት አድራሻ የሚኖሩበት መኖሪያ ቤት ኪራይ በተመከለተ ተሿሚዉ መኖሪያ ቤቱን በግሉ እንዲከራይ ለደረጃዉ የተፈቀደዉ የቤት ኪራይ አበል ደመዉዛቸዉ በሚከፈልበት ተቋም አማካይነት ከወር ደመወዝ ጋር አንድ ላይ የሚከፈል ይሆናል፡፡

5.6. የርዕሰ መስተዳደር፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳደሮችና በዚህ ደረጃ የተሾሙ የስራ ኃላፊዎች ፕሮቶኮል፣ የቤት ዉስጥ ቁሳቁስ፣ መስተንግዶ፣ የቤት ጥገና፣ የመብራትና ውሃ ፍጆታ እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ በመንግስት የሚሸፈን ሆኖ ዝርዝሩ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

5.7. የዞንና ልዩ ወረዳ ምክትል አፈ-ጉባኤዎች፣ የመምሪያ ኃላፊዎች፣ በመምሪያ ሀላፊ ደረጃ ተሿሚዎች፣ የወረዳ አስተዳደሪዎች፣ ከንቲባዎች የመኖሪያ ቤት ተከራይተው ሊኖሩ የሚችሉበት በየወሩ ግብር የማይጣልበት ብር 2,000.00 (ሁለት ሺ.ህ) የቤት ኪራይ አበል ከደሞዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

5.8. ምክትል መምሪያ ሀላፊዎች፣ በምክትል ማዕረግ ተሿሚዎች፣ የልዩወረዳ፣ የወረዳ፣ ከተማ አስተዳደር ተቋማት ጽ/ቤት ሀላፊዎች፣ ምክትል ጽ/ቤት ሀላፊዎች፣ ምክትል ከንቲባዎች፣ ምክትል አፈጉባኤዎች ለቤት ክራይ የሚሆን ግብር የማይጣልበት ብር 1000 (አንድ ሺ.ህ) በየወሩ ከደሞዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

5.9. የመኖሪያ ቤት ክራይ ክፍያ የክራይ ግሽበትን ለመከላከል ብዝሃ ከተሞች በሊዝ ህግ መሰረት አመራሩ መኖሪያ ቤት ሰርቶ መኖር እንዲችል እንዲሁም መንግስት መኖሪያ ቤትን እንዲያመቻች ባጠረ ጊዜ ዉስጥ መሬት አዘጋጅተዉ ያቀርባሉ፡፡ የክልሉ መንግስትም አቅም በፈቀደ መጠን ባጠረ ጊዜ ዉስጥ የመንግስት መኖሪያ ቤቶችን ያመቻቻል፡፡

## 6. ትራንስፖርት

6.1. ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሁለት ባለ አራት እግር ተሽከርካሪና ለቤተሰቦቻቸው አገልግሎት የሚውል 1 አውቶሞቢል ይመደብላቸዋል፡፡ እንዲሁም ከፀጥታና ደህንነት አንፃር እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች መኪናዎች በተጨማሪነት ሊሠማሩ ይችላሉ፡፡

6.2. ለክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ ለብሔረሰቦች ምክር ቤትና ለክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎች እና ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አንድ ባለአራት እግር ተሽከርካሪና ለቤተሰቦቻቸው አገልግሎት የሚውል 1 አውቶሞቢል ይመደብላቸዋል፡፡

6.3. የክልሉ ካቢኔ አባላት ቢሮ ኃላፊዎች፣ በካቢኔ ደረጃና ማዕረግ የተሾሙ የሥራ ኃላፊዎች፣ ለዞንና ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ፣ የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ብሄረሰቦች ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤዎች፣ የዞንና ልዩ ወረዳ አፈ-ጉባኤዎች፣ የዞንና ልዩ ወረዳ ምክትል አስተዳደሪዎች፣ ምክትል ቢሮ ሀላፊዎች፣ በክልል ምክትል ቢሮ ሀላፊ ደረጃ የተሾሙ የሥራ ኃላፊዎች ለሥራቸው የሚያገለግል በይዞታቸው

ሥር ሆኖ የሚጠቀሙበት አንድ ባለአራት እግር ተሽከርካሪ እንደየመስሪያ ቤቱ ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ የቢሮ ሀላፊዎች (ካቢኔ አባላት) እና በቢሮ ሀላፊ ደረጃ ለተሾሙ ሀላፊዎች እንደሁኔታዉ አቅም በፈቀደ መጠን ለቤተሰቦቻቸዉ የሚሆን አዉቶሞቢል የቤት መኪና ተጨማሪ ሊመደብላቸዉ ይችላል፡፡

6.4. ሌሎች የክልሉ ተሿሚዎች ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ እንደሁኔታው ሊኖራቸው ይችላል፡፡

7. የስልክ አገልግሎት

7.1. የመኖሪያ ቤት ስልክ

የተሿሚዎች የመደበኛ ስልክ ለሀገር ዉስጥ ጥሪ ፍጆታ በሚከተለዉ ሁኔታ ይከፈላቸዋል፡-

ሀ. ርዕሰ መስተዳድር፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ የብሄረሰቦች ምክር ቤት እና የክልል ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎች በመኖሪያ ቤታቸው ለሚጠቀሙበት ለመደበኛ ስልክ ፍጆታ በሚቀርብ ቢል መሠረት ይወራረዳል፡፡

ለ. የክልል ካቢኔ አባላት ቢሮ ኃላፊዎች፣ በክልል ካቢኔ ደረጃና ማዕረግ የተሾሙ የሥራ ኃላፊዎች፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪዎች በመኖሪያ ቤታቸው ለሚጠቀሙበት መደበኛ ስልክ በወር እስከ 300 (ሶስት መቶ) የስልክ አገልግሎት ወጪ ይሸፈንላቸዋል፣

ሐ. የሥራ ባህሪያቸው አስገዳጅ ለሆኑ መስሪያ ቤት ኃፊዎች የመደበኛ ስልክ ወጪ በርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ሲፈቀድ በቢል በሚቀርብ ሂሳብ መሠረት ሊወራረድ ይችላል፡፡

7.2. የተንቀሳቃሽ ስልክ እና የኢንቴርኔት ወርሃዊ ፍጆታ

የክልሉ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች በተንቀሳቃሽ ስልክ ለሚደረግ የሃገር ውስጥ ጥሪ የስልክ እና የኢንቴርኔት አገልግሎት በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይከፈላቸዋል፡፡

ሀ. ለርዕሰ መስተዳድር፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ የብሔረሰቦች ምክር ቤት እና የክልል ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎች ለተንቀሳቃሽ ስልክ ቴሌ ኮሙንኬሺን በሚሰጠዉ መስመር የሚጠቀም ሆኖ የፍጆታ ወጪዉ በሚቀርበው ቢል መሠረት የሚወዳደቅ ይሆናል፡፡ የኢንቴርኔት ፍጆታ በየወሩ በቢል ይከፈላቸዋል፡፡

ለ. የክልል ካቢኔ አባላት ቢሮ ኃላፊዎች፣ በክልል ካቢኔ ደረጃና ማዕረግ የተሾሙ ተሿሚ የሥራ ኃላፊዎች፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪዎች ከቴሌ ኮሙኒኬሽን በሚሰጥ መስመር የሚጠቀሙ ሆኖ ወርሃዊ ፍጆታ በሚቀርበዉ ቢል የሚወራረድ ይሆናል፡፡ ከሀገር ወጭ የተደረገ ጥሪ ካለ በኦዲተር እየተጣራ በሀላፊዉ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

Central ... Regional
State Office of the President

ለእንቴርኔት ፍጆታ በወር ከብር 800.00 (ስምንት መቶ) ብር ከደመውዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

ሐ. ምክትል ቢሮ ሀላፊዎች፣ በምክትል ቢሮ ሀላፊ ደረጃ የተሾሙ ሀላፊዎች፣ የብሔረሰቦች ምክር ቤት እና የክልል ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤዎች፣ የልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች፣ የዞን ምክትል አስተዳዳሪዎች፣ የዞን አፈ-ጉባኤዎች ለወርሃዊ ተንቀሳቃሽ ስልክ ፍጆታ ብር 1,000 (አንድ ሺ.ህ) ይከፈላቸዋል፡፡ እንዲሁም ለኢንቴርኔት ፍጆታ በወር 600 ብር ከደመውዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

መ. የዞን ምትክል አፈ-ጉባኤዎች፣ ዞን መምሪያ ሀላፊዎች፣ የወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ የከተማ ከንቲባዎች፣ የወረዳና ከተማ አስተዳደር ዋና አፈ-ጉባኤዎች ለወርሃዊ ለተንቀሳቃሽ ስልክ ፍጆታ ብር 500 (አምስት መቶ) ይከፈላቸዋል፡፡

ረ. የልዩ ወረዳ ምክትል አስተዳዳሪዎች፣ ዋና አፈ-ጉባኤዎች፣ ለተንቀሳቃሽ ስልክ ፍጆታ በየወሩ ብር 500 (አምስት መቶ) ከደመወዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

ሰ. የልዩ ወረዳ ምክትል አፈ-ጉባኤዎች፣ ካቢኔ አባላትና በካቢኔ ደረጃ ተሿሚዎች፣ ምክትል ጽ/ቤት ሀላፊዎችና ተመሳሳይ ሹመት ለተንቀሳቃሽ ስልክ ፍጆታ በወር ብር 400 (አራት መቶ) ከደመወዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

ቀ. ምክትል መምሪያ ሀላፊዎች እና በዚህ ደረጃ የተሾሙ ሀላፊዎች፣ የወረዳ ምትክል አስተዳዳሪዎች፣ ምትክል አፈ-ጉባኤዎች፣ ከተማ ምትክል ከንቲባዎችና ምክትል አፈ-ጉባኤዎች እንዲሁም በዛ ደረጃ የተሾሙ ሀላፊዎች፣ በወረዳና ከተማ አስተዳደር ካቢኔ አባላት፣ ምክትል ጽ/ቤት ሀላፊዎች ለወርሃዊ የስልክ ፍጆታ ብር 400 (አራት መቶ) ከደመወዛቸዉ ጋር ይከፈላቸዋል፡፡

**7.3. የስልክ ቀፎ፣ ላፕቶፕና የገመድ አልባ ተንቀሳቃሽ የእንቴርኔት አፓራተስ(ድቫይስ) በተመለከተ**

1. ለርዕሰ መስተዳደር፣ ለምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ ለአፈ-ጉባኤዎች፣ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የክልሉ ፋይናንስ አቅምና የወቅቱን ገበያ ዋጋ ባገናዘበ ሁኔታ ለአንድ ጊዜ የማይመለስ ዘመናዊ የስልክ ቀፎ፣ ላፕቶፕ እና ተንቀሳቃሽ የገመድ አልባ ኢንተርኔት ድቫይስ ተገዝቶ ይሰጣቸዋል፡፡ የተንቀሳቃሽ ገመድ አልባ ኢንተርኔት ወጪ በቢል ይወዳደቃል፡፡ በአይነት የሚገዙትን በተመለከተ የገንዘብ ጣሪያና ሌሎችን በተመለከተ ዝርዝሩ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

2. ለምክትል አፈ-ጉባኤዎች፣ ለቢሮ ሀላፊዎች ፣ በቢሮ ሀላፊ ደረጃ ለተሾሙ ሀላፊዎች፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ለዞን አስተዳዳሪዎች የክልሉ የፋይናንስ አቅምና የወቅቱን ገበያ ዋጋ ባገናዘበ ሁኔታ ለአንድ ጊዜ የማይመለስ ዘመናዊ የስልክ ቀፎ፣ ላፕቶፕ እና ተንቀሳቃሽ የገመድ አልባ ኢንተርኔት ድቫይስ ተገዝቶ ይሰጣቸዋል፡፡ ለተንቀሳቃሽ ገመድ አልባ ኢንተርኔት ወጪ በየወሩ ብር 1000 (አንድ ሺ.ህ)

ይከፈላቸዋል፡፡ በአይነት የሚገዙትን በተመለከተ የገንዘብ ጣሪያና ሌሎችን በተመለከተ ዝርዝሩ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

3. ምክትል ቢሮ ሀላፊዎች፣ በምክትል ቢሮ ሀላፊ ደረጃ የተሾሙ ሀላፊዎች የክልሉ ፋይናንስ አቅምን ባገናዘበ ሁኔታ ለአንድ ጊዜ የማይመለስ ላፕቶፕና የተንቀሳቃሽ ስልክ ቀፎ ተገዝቶ ይሰጣቸዋል፡፡

4. በንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የተገዙ ዕቃዎች ተሿሚዉ በሀላፊነት ላይ እያለ ከራሱ ጥፋት ዉጭ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቢበላሽ የተበላሸዉን ለተቋሙ በመመለስ አዲስ ይገዛለታል፣ ቢጠፋ፣ ቢሰረቅ ስለመጥፋቱ ወይም ስለመሰረቁ በሚመለከተዉ የህግ አካላት ሲረጋገጥ የማይመለስ ተለዋጭ ይገዛለታል፡፡

7.4. ወርሃዊ የስልክ ፍጆታ ስለሚሸፈንላቸው ሠራተኞች

ከዚህ በታች የተመለከቱት የግል የተንቀሳቃሽ ስልክ መስመርና ቀፎ ኖሯቸው ወርሃዊ የስልክ ፍጆታ የሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ. ለርዕሰ መስተዳድር እና ምክትል ርዕሰ መስተዳደር፣ ለህዝብ ተወካዮች እና ለብሔረሰቦች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዎች ሾፌሮች፣ አጃቢዎች እና ኤክስክዩቲቭ ሴክሬተሪዎች በየወሩ የብር 100 (አንድ መቶ) የሞባይል ካርድ እየተገዛ ይሰጣቸዋል፡

ለ. ለክልል ለክልል ካቢኔ አባላት ቢሮ ኃላፊዎች እንዲሁም በቢሮ ኃላፊ ደረጃና ማዕረግ ለተሾሙ የሥራ ኃላፊዎች ሾፌሮች፣ ፀሐፊዎች በየወሩ የብር 50 (ሃምሳ ብር) የሞባይል ካርድ እየተገዛ ይሠጣቸዋል፡፡

ሐ. በተሿሚ /ሠራተኛ የሥራ ኃላፊነት ላይ ተወክሎ የሚሠራ ባለሙያ በቦታው ከሁለት ወር በላይ በውክልና የሚቆይ ከሆነ የተፈቀደውን የተንቀሳቃሽ ስልክ አበል ብቻ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ውክልናው ሲነሳ የሚያገኘው ጥቅም የሚቋረጥ ይሆናል፡፡

## 8. የተሿሚ ሀላፊዎች የአልጋ አበል

8.1. ለርዕሰ መስተዳደር፣ ለምክትል ርዕሰ መስተዳደሮች፣ ለአፈ-ጉባኤዎች፣ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ከተፈቀደላቸዉ ዉሎ አበል ላይ 40% ተቀንሶ በማንኛዉም ሆቴል አድረዉ በደረሰኝ ይወዳደቅላቸዋል፡፡

8.2. ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ለብሄረሰቦች ምክር ቤትና ለክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤዎች፣ ለቢሮ ሀላፊዎች ፣ በቢሮ ሀላፊ ደረጃ ለተሾሙ ሀላፊዎች፣ ለዞን አስተዳዳሪዎች ከዉሎ አበል ላይ 40% ለአልጋ ተቆራጭ ተደርጎ እስከ ባለ አራት ኮከብ ሆቴል አድረዉ በደረሰኝ ይወራረዳል፡፡

8.3. ምክትል ቢሮ ሀላፊዎች፣ በማንኛዉም ተቋም በምክትል ቢሮ ሀላፊ ደረጃ/ማዕረግ የተሾሙ የስራ ሀላፊዎች፣ ምክትል የዞንና ልዩ ወረዳ አስተዳዳሪዎችና በዚያ ደረጃ የተሾሙ የስራ ሀላፊዎች፣ የዞን አፈ-ጉባኤዎች ከተፈቀደዉ የዉሎ አበል ላይ 40% ተቀንሶ እስከ ባለሶስት ኮከብ ሆቴል አድረዉ በደረሰኝ ይወራረዳል፡፡

8.4. የሀላፊዎች ሾፌሮቻቸዉና አጃቢዎቻቸዉ የደሞዝ መጠናቸዉን መሰረት ተደርጎ ከሚከፈለዉ አበል ላይ 40% ተቀናሽ ተደርጎ ሀላፊዎቻቸዉ በዚህ ደንብ ተፈቅዶላቸዉ ባደሩበት ባለኮከብ ሆቴል ባለአንድ አልጋ ክፍል አድረዉ በሚያቀርቡት ደረሰኝ መሰረት እዲወራረድላቸዉ ይደረጋል፡፡

8.5. በዚህ ክፍል ለተሿሚዎች የሚከፈለዉ ገንዘብ ወይም የሚሸፈንለት ወጪ ከግብር ነፃ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሥራ ሁኔታዎች

### 9. የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት

#### 9.1. የህክምና አገልግሎት

ሀ. ርዕሰ መስተዳድር፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና በዚያ ደረጃ የተሾሙ ስራ ሀላፊዎች በፌዴራል መንግስት ለሚኒትሮች በተፈቀደው መሠረት የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ለ. ሁለቱም የክልል ዋና አፈ-ጉባኤዎች፣ የክልል ካቢኔ አባል ቢሮ ኃላፊዎች፣ በካቢኔ ቢሮ ሀላፊ ደረጃ/ማዕረግ የተሾሙ የስራ ሀላፊዎች፣ የዞን አስተዳዳሪዎች በፌዴራል መንግስት ለሚኒስተር ደኤታዎች በተፈቀደው መሠረት የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ሐ. ርዕሰ መስተዳድር እና ምክትል ርዕሰ መስተዳሮች፣ ሁለቱም የክልል ዋና አፈ-ጉባኤዎች፣ የክልል ካቢኔ አባል ቢሮ ኃላፊዎች፣ በካብኔ ቢሮ ሀላፊ ደረጃ/ማዕረግ የተሾሙ የስራ ሀላፊዎች፣ የዞን አስተዳዳሪዎች የትዳር ጓደኞቻቸውና ዕድሜያቸዉ 18 ዓመት ላልሞላቸዉ ልጆቻቸው በሀገር ውስጥ በሚገኝ ደረጃውን በጠበቀ በመንግስት የህክምና ተቋም የሚሠጠውን ማንኛውም የህክምና አገልግሎት ወጪ በመንግስት ይሸፈናል፡፡

መ. በዚህ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ-ሐ) ከተገለፁት ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ውጭ ከወረዳ እስከ ክልል የተሾመዉ ማንኛውም የመንግስት ተሿሚዎች፣ የትዳር ጓደኛውና ዕድሜያቸዉ 18 ዓመት ያልደረሱ ልጆቹን በሀገር ውስጥ በሚገኝ ደረጃውን በጠበቀ በመንግስት የህክምና ተቋም የሚሰጠው ማንኛውም የህክምና አገልግሎት ወጪ በመንግስት ይሸፈናል፡፡

ሠ. ተሿሚው ወይም የትዳር አጋሩ ወይም 18 ዕድሜ ያልሞላዉ ልጅ ከመንግስት ሆስፒታል ወደ ሌላ የግል ሆስፒታል መታከም እንዳለበት እንዲሁም ከመደበኛ መኖሪያ ቦታው ወደ ሌላ ስፍራ ሄዶ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ሲያስፈልግና ይህም በመንግስት ሆስፒታል የሕክምና ዶክተር ተረጋግጦ በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ሲፈቀድ ተሿሚው የሕክምና ተቋም ወደሚገኝበት ሲሄድ ለማጓጓዣ፣ በህክምና ለሚቆይበት ጊዜ ውሎ አበል እና የታማሚዉ ህክምና ወጪ ይሸፈንለታል። ታማሚዉ ተኝቶ ታካሚ ከሆነ ግን ተኝቶ ለሚቆበት ጊዜ አበል አይከፈለዉም።

### 9.2. በሥራ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት

ሀ. በስራ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለመንግስት ሰራተኞች ጡረታ ለመደንገገድ የወጣ አዋጅ ቁጥር 1267/2014 ክፍል 7 አንቀፅ 28 የተደነገገው ለዚህም ተፈፃሚ ይሆናል።

ለ. በዚህ ንዑስ አንቀፅ በፊደል ተራ ‹‹ሀ›› የተመለከተው ቢኖርም ተሿሚው ሆን ብሎ በተለይም በመስሪያ ቤቱ አስቀድሞ በግልፅ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች በመጣስ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሰክሮ በስራ ላይ በመገኘቱ የደረሰበት ጉዳት በስራው ምክንያት እንደደረሰ ጉዳት አይቆጠርም።

ሐ. በስራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የመንግስት ተሿሚ የሚያስፈልገውን የህክምና ወጪ በመስሪያ ቤቱ ይሸፈናል።

መ. በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የመንግስት ተሿሚ ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራ እስኪመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቄታው መስራት የማይችል መሆኑ በህክምና ማስረጃ እስከሚረጋገጥ ድረስ የህመም ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ጋር ይሰጠዋል። ሆኖም የሚሰጠው የህመም ፈቃድ በማናቸውም ሁኔታ ከ12 ወራት አይበልጥም።

ሠ. በአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስት ከጉዳቱ ድኖ ወደ ስራ መመለስ ያልቻለ ተሿሚ በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀፅ 10.3 የተደነገጉ ጥቅማ ጥቅሞች ይጠበቁለታል።

ረ. ተሿሚው ሕክምናውን በአግባቡ ባለመከታተሉ ወይም በህክምና የተሰጠውን ትእዛዝ ባለማክበሩ ህክምናውን ያጓተተ መሆኑ በሚመለከተው የህክምና ባለሙያ የተረጋገጠ እንደሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ‹‹መ›› መሠረት የሚሰጠው የህክምና ፈቃድ ይቋረጣል።

### 9.3. በሥራ ላይ ለደረሰ ጉዳት ጡረታና ካሳ ክፍያ

ሀ. ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል የመስራት ችሎታ ያጣ ተሿሚ የጡረታ መዋጮ እየከፈለ ያለ ከሆነ አግባብ ባለው ጡረታ ህግ የተሰጠው መብት ይጠበቅለታል።

Central ... State ... Regional ... President

ለ. በሥራ ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ዘላቂ ሙሉ የመስራት ችሎታውን ያጣ የመንግስት ተሿሚ ስለመንግስት ሠራተኞች የጡረታ ሁኔታ ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 1267/2014 መሠረት የጡረታ መብት የሚከበርለት ይሆናል፡፡

ሐ. ተሿሚው በደረሰበት ጉዳት ምክንያት የሞተ እንደሆነ ለህጋዊ ወራሾች ስለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ለመደንገግ በወጣ አዋጅ ቁጥር 1267/2014 መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

መ. ከሦስተኛው ወገን ስለሚጠየቅ የካሳ ክፍያ

1. በተሿሚው ላይ የደረሰው ጉዳት በሦስተኛ ወገን ጥፋት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ መስሪያ ቤቱ በጉዳት ምክንያት ለተሿሚው ባወጣው ወጪ መጠን ጉዳቱን ካደረሰው ወገን ካሳ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡
2. ተሿሚው ጉዳቱን ካደረሰበት ወገን ካሳ የተቀበለ እንደሆነ መስሪያ ቤቱ በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀፅ 10.2 ‹‹ሐ›› ላይ በተደነገገው መሠረት ያወጣውን ወጪ ከተሿሚው ደመወዝ ላይ ሊቀንስ ይችላል፡፡

**9.4. ከግብር ነፃ ስለመሆን**

በዚህ ደንብ አንቀፅ 10.3 መሠረት የሚደረግ ክፍያ ከግብር ነፃ ይሆናል፡፡ እንዲሁም በእዳ ሊከበር ወይም በማቻቻያነት ሊቀነስ ወይም ባለመብቱ ሊያስተላልፈው አይችልም፡፡

**10. .የወሊድ ፈቃድ**

ማንኛዋም ነፍሰ ጡር የሆነች የመንግስት ተሿሚ በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ላይ የተቀመጡ መብቶች ተጠቃሚ ትሆናለች፡፡

**11. የህመም ፈቃፍ**

11.1. ማንኛውም የመንግስት ተሿሚ በህመም ምክንያት ስራ መስራት ያልቻለ እንደሆነ የህመም ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

11.2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 12.1 መሠረት ለተሿሚው የሚሰጥ የህመም ፈቃድ በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ቢወስድም ህመም ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው በአስራ ሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ ከስምንት ወር አይበልጥም፡፡

11.3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 12.2 መሠረት የሚሰጥ የህመም ፈቃድ ለመጀመሪያ ሶስት ወራት ከሙሉ ደመወዝ ጋር ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት ከግማሽ ደመወዝ ጋር እና ለመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት ያለደመወዝ ይሆናል፡፡

11.4. የታመመው ተሿሚ ቦታ መስተዳድሩ ሌላ ኃላፊ ለመመደብ በሚፈለግበት ጊዜ በመንግስት መስሪያ ቤት ተሿሚው በሚያሟላበት ቦታ ምደባ እንዲሰጠው

ይደረጋል፡፡ ጥቅሙን በተመለከተ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት ይወሰናል፡፡

12. የጋብቻ ፈቃድ

ማንኛውም የመንግስት ተሿሚ ሲያገባ ሦስት የሥራ ቀናት የጋብቻ ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

13. .የሐዘን ፈቃድ

ማንኛውም የመንግስት ተሿሚ የትዳር ጓደኛ ተወላጅ ወይም እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ ወይም የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበት እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት የሦስት ተከታታይ ቀናት ሃዘን ፈቃድ ይሰጠዋል

14. የፈተና ፈቃድ

አንድ ተሿሚ ስራ ላይ እያለ እንዲማር የተፈቀደለት ከሆነና ፈተና ላይ ስለመሆኑ ከሚማርበት ወይም ፈተናውን ከሚወስድበት አካል ማስረጃ ሲያቀርብ ፈተና ለሚወስድባቸው ቀናት ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

15. ከደመወዝ ጋር ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ

ማንኛውም የመንግስት ተሿሚ፡-

ሀ. ከፍርድ ቤት ወይም ከሌሎች ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት መጥሪያ ሲደርሰው የተጠራበት ጉዳይ እስከ ሚያበቃበት ጊዜ ድረስ፣

ለ. በሕዝብ ምርጫ ስልጣን የሚይዝ የመንግስት ኃላፊዎች ለመምረጥ ወይም ለመመረጥ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሲሆን ምርጫ ቦታ ወይም ቅስቀሳ ለሚወስድበት ጊዜ ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

16. በሞት ምንያት አገልግሎቱ ሲቋረጥ ስለሚፈፀም ክፍያ

አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግስት ተሿሚ በሞት ምክንያት አገልግሎቱ ሲቋረጥ በሕይወት ሳለ ለመስሪያ ቤቱ በፅሁፍ ላሳወቃቸው የትዳር ጓደኛው ወይም በስሩ ይተዳደሩ ለነበሩ ቤተሰቦቹ የሦስት ወር ደመወዝ ይከፈላል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለተሿሚዎች የትምህርት ዕድል

**17. ከሹመት ተነስተው ወደ ትምህርት ቤት የሚገቡ ሀላፊዎችን በተመለከተ**

17.1. በየመዋቅሩ በአመለከካታቸው፣ በተግባራቸውና በሥነ-ምግባራቸው ግንባር ቀደም እና ውጤታማ የሆኑ እንዲሁም ለተራዘመ ጊዜ ለህዝቡ በታማኝነት ያገለገሉ አመራሮች ከየአስተዳደር እርከኑ እንደየአስፈላጊነቱ ተመልምለው የሀገር ዉስጥም ሆነ የሀገር ዉጪ የትምህርት እድል ይሰጣቸዋል። ከሀገር ዉጭ ትምህርት ዕድል የማበረታቻን፣ ብዝሃነትን እና የመንግስትን የገንዘብ ዐቅም ባገናዘበ ሁኔታ በርዕሰ መስተዳደሩ ታይቶ በሚፈድ መሰረት ይሆናል።

17.2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 18.1 ድንጋጌ መሠረት የተመለመሉ አመራሮች በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መሠረት የትምህርት ዕድል ሲሰጣቸው እና ትምህርት ቤት ሲገቡ ለትምህርት ዓላማ የተነሱበት ኃላፊነት ደመወዝ የሚያገኙ ሲሆን ከስልክ ፍጆታ ወጪ ያሉ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከፈላቸውና የትምህርት ወጪያቸውም በመንግስት በኩል ተሸፍኖ እንዲማሩ ይደረጋል።

17.3. በዚህ ሁኔታ ተመልምላዉ በአሁኑ ሰዓት ትምህርት ላይ ያሉ አመራር ይህ ደንብ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተጠቃሚ ይሆናሉ፣

17.4. ለትምህርት ተፈቅዶላቸዉ የሚሄዱ ተሿሚ ሀላፊዎች ክፍያቸዉ በነበሩበት ተቋማቸዉ በጀት ተይዞላቸዉ የሚፈጸም ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## ከሀላፊነት ስለመነሳት

**18. ከሹመት የሚሰናበቱ ኃላፊዎችን በተመለከተ**

18.1. ማንኛውም የመንግስት ተሿሚ በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ሊያቋርጥ ወይም ለማቋረጥ ሲጠይቅ ሲያከናውን የነበረውን የሥራ ዓይነት፣ የአገልግሎት ዘመኑን፣ ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝ እና ከስራ የተሰናበተበትን ምክንያት የሚገልፅ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

18.2. በሹመት ላይ የነበረ ኃላፊ ከሹመት ሲነሳ በአንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 20.1፣20.2 እና 20.3 የተመለከቱት ነጥቦች የማይመለከቱትና በመንግስት ሠራተኝነት ሊመደብ የሚችል መሆኑን ከሹመት ካነሳው አካል የማረጋገጫ ደብዳቤ ሲያቀርብ በየአስተዳደር እርከኑ በሚገኙ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ፣ መምሪያ ጽ/ቤትና ዩኒት አማካይነት ምደባ እንዲሰጠው ይደረጋል።

18.3. በተለያየ ምክንያት ከሹመት ላይ የሚነሱ ኃላፊዎች ከኃላፊነታቸው እንደተነሱ ወዲያውኑ ምደባ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆነ ምንያት ምደባ ሳያገኙ ቢቆዩ ክፍት የሥራ መደብ ሲገኝ ምደባው የሚሰጣቸው ከኃላፊነታቸው ከተነሱበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን ምደባ እስካልተሰጣቸዉ ድረስ ለ 3 ወር ያህል ጊዜ ድረስ ከሹመት በፊት ሲያገኙ የነበሩት ደሞዝና ጥቅማጥቅም ከሀላፊነት በተነሱበት ተቋም አማካይነት እየተከፈለ ይቆያል፡፡ እስከ 3 ወር ድረስ ምደባ ካልተሰጠ/ጣት የመመደብ ሀላፊነት ያለበት አካልን ተጠያቂ ማድረግና የመንግስትን ወጭ ከተጠያቂዉ አካል የማስመለስ መብት ኖሮት የተሰናባቹ ደመውዝና ጥቅማጥቅም ግን አይቆምም፡፡

18.4. ከሹመት የተነሳውን ባለሙያ ክፍት የሥራ መደብ መኖሩና የሥራ መደቡ የሚጠይቀውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ መስፈርት ማሟላቱ እየተረጋገጠ ይመደባል፡፡ ለተመደበበት የሥራ መደብ የተፈቀደውን ደመወዝ ይከፈለዋል፡፡

18.5. ከሹመት በመነሳት ምክንያት ምደባ የሚሰጠው ባለሙያ አሁን የተመደበበት የሥራ መደብ መነሻ ደመወዝ ከመሾሙ በፊት በሜሪት ሥርዓት ተመድቦ ሲከፈለው ከነበረው ደመወዝ ያነሰ ከሆነ ከመሾሙ በፊት ሲያገኝ የነበረው ደመወዝ ወይም በሜሪት መደቡ ቢቆይ አሁን ሊደርስ የሚችለዉ መደብ ደሞዝ ይከፈለዋል፡፡

18.6. ቀደም ሲል የመንግስት ሠራተኛ ሳይሆን ከትምህርት ተቋማት ተመርቀው በቀጥታ በኃላፊነት የሚመደቡ ተሿሚዎች ወይም ከሹመት በፊት የመንግስት ሠራተኛ ያልነበሩ የምክር ቤት አባላት እንደየቅደም ተከተላቸው ከሹመት ሲነሱ ወይም የአባልነት ጊዜአቸውን አጠናቀው በክብር ሲሰናበቱና በመንግስት ሠራተኞች እንዲመደቡ ሲወሰን ከሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ፀድቆ በተላለፈውና በመስሪያ ቤቱ በክፍትነት በተያዘው የሥራ መደብ የሚጠይቀውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ የሚያሟሉ መሆኑ እየተረጋገጠ የሚመደቡ ሲሆን በተመደቡበት መስሪያ ቤት በሰው ሃብት ስራ አመራር የማሟላት አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የቅጥር ፎርማሊቲ ተሟልቶ መረጃው ለሚመለከተው አካል መቅረብ አለበት፡፡

18.7. የጡረታ መለያ ቁጥር ሳይኖራቸውም ሆነ በቅጥር አፈፃፀም ስርዓት ሳይፈፅሙ የጡረታ አበል በመክፈል ላይ የሚገኙ ተሿሚዎች በመንግስት ሠራተኛ አስተዳደር አዋጅና አግባብ ባለው የህግ መሠረት አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላት ተገቢው ይፈፀማል፡፡

**19. በመንግስት ሠራተኝነት የማያስመድቡ ምክንያቶች**

19.1. የአቅም ችግር ባልሆነ ምክንያት ሆን ብሎ በተሾመበት ተቋም ውስጥ ሥራን በድሎ የወረደ ከሆነ፣

19.2. በሙስና ሊያስጠይቀዉ የሚያስችል ጥፋት የፈፀመ ከሆነ እና በሕግ የሚፈለግ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

19.3. ሹመት የሰጠዉን አካል ሳያስፈቅድ በራሱ ጊዜ ከመንግስት ሹመት የለቀቀ ከሆነ መንግስት የሥራ ምደባ የመስጠት ግዴታ የለበትም፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

20. በልዩ ደንብ የታየባቸው መስሪያ ቤቶች ማለትም የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፍትህ ቢሮ፣ የገጠር መንገዶች ባለስልጣን ኃላፊዎች በልዩ ደንባቸዉ በተቀመጠው አሠራር መሠረት የሚፈፀም ሆኖ በዚህ ደንብ የተደነገገዉ የተሻለ ከሆነ ተጠቃሚ ይሆናሉ ፡፡

21. በክልል ደረጃ መስሪያ ቤቶች ወስጥ የሚሠሩና ከሥራ ባህሪያቸው የተነሳ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች የሚያስፈልጋቸው ሆኖም በዚህ ደንብ ውስጥ በግልፅ ያልተሸፈኑ አካላት መኖራቸው ተረጋግጦ በበጀት የተደገፈ ጥያቄ ከመስሪያ ቤቶች ሲቀርብ ወይም የሥራ ኃላፊነታቸው ክብደትና ስፋት በዚህ ደንብ ከተደነገገው የወርሃዊ ፍጆታ ጣሪያ በላይ የሚጠይቅ መሆኑ ታምኖበት ጥያቄው በተመሳሳይ መልኩ በበቂ ማስረጃ ተደግፎ ለዚህ ደንብ አውጪ አካል ሲቀርብ አስፈላጊው ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡ ሆኖም ከተደነገገው አሰራር ውጭ ተፈፅሞ ቢገኝ እንዲፈፀም ያዘዘው ኃላፊ ወይም ተወካይ በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

22. የኢንቴርኔት አፓራተስ ብልሽት ከመስመር ጋር የተያያዘ ከሆነ ችግሩን መስመሩን ለሸጠው ለቴሌኮሚኒኬሽን መስሪያ ቤት ማስታወቅ ይገባል፡፡ ሆኖም ከተረከበው ኃላፊ እጅ ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ አገልግሎት መስመሩን በተመለከተ ሁኔታውን ወዲያውኑ ለቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት ማስታወቅ የሚገባ ሲሆን መስመሩን በድጋሚ ለማውጣት የሚያስፈልገው ወጪ በግለሰቡ ይሸፈናል፡፡

23. በዚህ ደንብ የተፈቀዱ የጥቅማ ጥቅሞች ወጪዎች ከመታዘዙ በፊት የተፈቀደ በጀት መኖሩን ማረጋገጥ ወይም አስቀድሞ በጀት እንዲያዝ ማስደረግ የየመስሪያ ቤቶቹ ኃላፊነት ነው፡

24. በዚህ ደንብ ላይ ያልተገለፁ ሌሎች ሊከበሩ የሚችሉ ጥቅማ ጥቅሞች በክልሉ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት ሊከበሩ ይችላሉ፡፡

25. ደንቡን የማሻሻልና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ይህ ደንብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ማሻሻል ይችላል፤ ደንቡን ለማስፈፀም የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

**26. የተሻሩ ሕጎችና ተፈፃሚነት ስለማይኖረዉ ህጎች**

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የተሿሚዎችን ጥቅማ ጥቅምና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን ለመወሰን የወጣው የወጣ ደንብ ቁጥር 108/2006 እና ከዚህ በፊት የነበሩ የጥቅማጥቅም ደንቦች፣ ደንብ ቁጥር 184/2012 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

2. ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛዉም ደንብ፣ መመሪያ፣ ዉሳኔ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡

**27. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመስከረም 1 ቀን 2016 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

እንዳሻው ጣሰዉ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
Central Ethiopia Regional State Office of the President